ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካቾች፡ 1. ወ/ሮ ሙሉእመቤት አምባቸው

2. አቶ መልኬ ይርጋ

ተጠሪ፡ ጉምሩክ ኮሚሽን ኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ 1ኛ አመልካች በዚህ መዝገብ ላይ፤ 2ኛ አመልካች ደግሞ በመ/ቁ/249323 ላይ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም በሁለቱም መዝገቦች ላይ የቀረበው የህግ ክርክር እና ማስቀረቢያ ነጥብ ተመሳሳይ በመሆኑ ሁለቱም መዝገቦች ቀድሞ በተከፈተው በዚህ መዝገብ ላይ ተጣምረው ተመርምረው ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ ለህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ማጓጓዥ ያነት ውሏል ከተባለ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ መወረስ ጋር ተያይዞ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የ1ኛ አመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/227926 ላይ ታህሳስ 04/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ፤ እንዲሁም የ2ኛ አመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/228134 ላይ ሚያዝያ 30/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበውም ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ጭነው ተገኝተዋል በተባሉት የአሁን አመልካቾች ተሽከርካሪዎች ላይ የውርስ ትዕዛዝ ለመስጠት አመልካቾች ስለተጫነው እቃ ምንነት የነበራቸውን እውቅና ማረጋገጥ አስፈላጊ አይደለም በሚል ምክንያት ተሽከርካሪዎቹ ተወርሰው ለመንግስት ገቢ እንዲሆኑ የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ከጦር መሳሪያ አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ

ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 21 እና 22 እንዲሁም ከጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 147 አንፃር መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡

ጉዳዩ እንዲህ ነው፡፡ ንብረትነቱ የአሁን 1ኛ አመልካች የሆነ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-A36589 አ/አ የሆነ አይሱዙ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ከጎንደር ወደ ቆቦ መስመር አራት ክላሽ የጦር መሳሪያን ጭኖ ሲያጓጉዝ ተይዟል እንዲሁም ንብረትነቱ የአሁን 2ኛ አመልካች የሆነ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-06286 አ/አ የሆነ አይሱዙ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ሶስት ህገ ወጥ የጦር መሳሪያዎችን ከጌሾ ጋር ቀላቅሎ ሲያጓጉዝ ቱሉ ዲምቱ የጉምሩክ መቆጣጣሪያ ጣቢያ ላይ በተደረገ ፍተሻ የተያዘ መሆኑን ተጠቅሶ ሁለቱም ተሽከርካሪዎች በጦር መሳሪያ አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አነቀፅ 21/15/ መሰረት ውርስ ሆነው ለመንግስት ገቢ እንዲሆኑ በአሁን ተጠሪ ይወሰናል፡፡ አመልካቾች በየፊናቸው ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለተጠሪ መስሪያ ቤት ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ቀጥሎም ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት ባለማግኘቱ በተለያዩ መዝገቦች ላይ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በአመልካቾች በተናጠል በተከፈተው መዝገብ ላይ የአሁን ተጠሪን አስቀርቦ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ መስሪያ ቤትም ሆነ የፌዴራል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የአሁን አመልካቾች ተሽከርካሪዎች የተጠቀሰውን የጦር መሳሪያ ጭነው የተገኙት በተሽከርካሪዎቹ ላይ በተገጠመ ባዕድ አካል/ሻግ/ ውስጥ ተደብቆ ባለመሆኑ እና የተሽከርካሪዎቹ ባለንብረቶች ስለተጫኑው ህገወጥ የጦር መሳሪያ ባላወቁበት ሁኔታ ወይም በድርጊቱ ተሳታፊ መሆናቸው ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ለመንግስት ውርስ ሊሆኑ ይገባል በማለት የሰጡት ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በሚል ውድቅ አድርጎ ተሽከርካሪዎቹ ለአሁን አመልካቾች እንዲመለሱ በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

ተጠሪ በተራው የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመቃወም በተለያዩ መዝገቦች ላይ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱም የአሁን አመልካቾችን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ህግ አዋጅ ቁጥር 1177/2012 እንጂ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ወይም ማሻሻያ አዋጁ 1160/2012 አይደለም፤ ለህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ማጓጓዥያነት የዋሉት የአመልካቾች ተሽከርካሪዎች የደረቅ ጭነት ማመላለሻ እንጂ የህዝብ ማመላለሻ ባለመሆናቸው ከአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 21/16/ ድንጋጌ አንጻር የሚታይ አይደለም፤ የጦር መሳሪያ ማጓጓዥያዎች በጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 21/15/ ድንጋጌ መሰረት የባለንብረቱን ማወቅ እንደመስፈርት የደነገገ ባልሆነበት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ህገ ወጥ የጦር መሳሪያዎቹ በተሽከርካሪዎቹ ላይ በተሰራ ባዕድ አካል/ሻግ/ ውስጥ ተደብቀው የተጓጓዙ መሆኑ አልተረጋገጠም እንዲሁም አመልካቾች ስለተጫነው እቃ ምንነት እውቀቱ የነበራቸው ወይም የወንጀሉ ተሳታፊ ስለመሆናቸው አልተረጋገጠም በሚል መወሰኑ ከህግ አግባብ ውጭ ነው በሚል ውድቅ አድርጎ የተጠሪ መስሪያ ቤት የተሰጠውን የውርስ ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ላይ ነው፡፡ 1ኛ አመልካች በዚህ መዝገባ ላይ ጥር 30/2015 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ቅሬታ፣ 2ኛ አመልካች ደግሞ በመ/ቁ/249323 ላይ ሰኔ 16/2015 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ቅሬታ በይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ተፈጽሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ በሁለቱ መዛግብት ላይ በአመልካቾች የቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርመሮ ከላይ በዚህ ፍርድ መግቢያ ላይ የተመለከተውን ነጥብ ግራ ቀኙ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ የየበኩላቸውን የጽሑፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘውን ማስቀረቢያ ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ይዘት መረዳት የተቻለው አመልካቾች ከስር ጀምሮ አጥብቀው የሚከራከሩት ተሽከርካሪያቸው የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ቢሆንም የሚንቀሳቀሱት በቀጠሯቸው አሽከርካሪዎቻቸው አማካኝነት በመሆኑ ስለተጫነው እቃ እውቀቱ ሳይኖራቸው ብዛት ያለው ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ጭነዋል ተብሎ መወረሳቸው አግባብ እንዳልሆነ፣ በተሽከርካሪዎቹ ላይ የውርስ ውሳኔ የሚሰጥ ቢሆን እንኳን በጦር መሳሪያ አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ ቁጠር 1177/2012 አንቀጽ 22/12/ ስር በተመለከተው አግባብ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቅፅ 147 ስር በተመለከተው የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት መሆን ይገባው ነበር በሚል ነው፡፡

በመሰረቱ የጦር መሳሪያ አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 እና 859/2006 የተለያዩ ጉዳዮችን የሚያስተዳድሩ እራሳቸውን የቻሉ ህጎጋት ከመሆናቸውም በላይ ለህጎቹ መውጣር የየራሳቸውን መነሻ ምክንያት ያላቸው ናቸው፡፡ የአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንዱ መሰረታዊ ዓላማ ኮንትሮባንድ እና ሌሎች የንግድ ማጭበርበር ወንጀሎች በህጋዊ የንግድ እንቅስቃሴ፣ በህዝብ ደህንነት፣ በመንግስት ገቢ እና በሌሎች ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገቶች ላይ የሚያስከትሉትንና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን አሉታዊ ተጽእኖ ለመከላከል የተጠናከረ የህግ ማስከበሪያ ስርዓት ለመዘርጋት እንደሆነ በአዋጁ መግቢያ ላይ ከሰፈረው መሰረተ ሀሳብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ለጦር መሳሪያ አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 መውጣት አንዱ ምክንያት ደግሞ ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር ከሚያስከትለው ጉዳት አኳያ የሀገርና ህዝብን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ እንዲሁም የዜጎችን እና የህዝቦችን መብትና ደህንነት ለማስከበር ስለመሆኑ በአዋጁ መግቢያ ላይ ተመላክቷል፡፡

ለሁለቱ አዋጆ መውጣት መሰረት ከሆኑት ከእነዚህ መሰረተ ሀሳቦች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው አዋጆቹ በጥቅሉ የህዝብን ሰላም እና ደህንነት የመጠበቅ እና የማረጋገጥ ዓላማን ያነገቡ ቢሆኑም በተናጠል ሊገዙት እና ሊያስተዳድሩት የተፈለገ ዝርዝር ዓላማ እና ተግባር ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ የአዋጅ ቁጥር

1177/2012 ዝርዝር ዓላማ እና ተግባር በአዋጁ ትርጓሜ መሰረት የጦር መሳሪያ ተብለው የተገለፁትን መሳሪያወች አያያዝ፣ አጠቃቀም እና አስተዳደር በተመለከከተ ስርዓት ማበጀት እና መቆጣጣር ሲሆን የአዋጅ ቁጥር 859/2012 ዝርዝር ዓላማና ተግባር ደግሞ የኮንትሮባንድና ህገ ወጥ የንግድ እንቅስቃሴን መቆጣጠር እና መልክ ማስያዝ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የተፈፀመው ህገ ወጥ ድርጊት ከጦር መሳሪያ ዝውውር ጋር የተያያዘ ከሆነ ጉዳዩ የሚገዛው በቀጥታ በሚመለከተው አዋጅ ቁጥር 1177/2012 መሰረት ይሆናል፡፡ በአንፃሩ የተፈፀመው ህገ ወጥ ድርጊት ኮንትሮባንድ እና ከህግ ወጥ የንግድ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ ከሆነ ጉዳዩ የሚገዛው በአዋጅ ቁጥር 859/2006 /በአዋጅ ቁጥር 1160/2012 እንደተሻሻለው/ መሰረት ይሆናል ማለት ነው፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ በአመልካቾች ተሽከርካሪዎች ላይ የውርስ ትዕዛዝ የተላለፈው ህገ ወጥ የጦር መሳሪያን ሲያጓጉዙ ተገኝተዋል በሚል ነው፡፡ ለተሽከርካሪዎቹ መወረስ ምክንያቱ ህገ ወጥ የጦር መሳሪያን ማጓጓዝ ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ የሚገዛው ስራ ላይ ባለው አዋጅ ቁጥር 1177/2012 መሰረት ይሆናል፡፡ በዚሁ አግባብ በአዋጁ እንዲሁም አዋጁ እውቅና ከሰጠው አሰራር ውጭ ሲንቀሳቀስ የተገኘ የጦር መሳሪ ከድርጊቱ ጋር በተያያዘ የተመለከተው የወንጀል ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ የጦር መሳሪያውም ሆነ መሳሪያውን ለሚጓጓዝ አገልግሎት ላይ የዋለ ተሽከርካሪ ወይም እንሰሳ ውርስ ተደርጎ ለመንግስት ገቢ እንደሚደረግ በአዋጁ አንቀፅ 21/15/ ስር ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ በጥቅሉ መረዳት የሚቻለው ህገ ወጥ የጦር መሳሪያን ለማጓጓዙ አገልግሎት ላይ የዋለ ማናቸውም ተሽከርካሪም ሆነ እንሰሳ በቀጥታ በሚሰጥ አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚወረስ መሆኑን ነው፡፡ ለዚህ ጥቅል አገላለጥ የተቀመጠው ልዩ ሁኔታ/በስተቀር/ በአዋጁ አንቀፅ 21/16/ ስር የተመለከተው ነው፡፡ ልዩ ሁኔታውም ለህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ማጓጓዥ ያነት የዋለው ተሽከርካሪ የህዝብ ማመላለሻ ከሆነ የተሽከርካሪው ባለቤት ስለድርጊቱ እንደሚያውቅ ወይም ስለድርጊቱ አውቆ አስፈላጊውን እርምጃ ሳይወስድ የቀረ መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር አልያም በተሽከርካሪው ላይ ባዕድ አካል ተሰረቶለት በዚያው ውስጥ ተደበቀ የተገኘ መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ተሽከርካሪው ሊወረስ አይገባም የሚል ነው፡፡ ከእነዚህ ሁለት ንዑሳን ድንጋጌዎች ይዘት መረዳት የሚቻለው ህገ ወጥ የጦር መሳሪያን ሲያጓጉዝ ከተገኘ ተሽከርካሪ ውርስ ጋር በተያያዘ ለአወራረስ ውሳኔው የባለንብረቱ እውቅና የሚፈለገው ለማጓጓዥ ያነት የዋለው ተሽከርካሪ የህዝብ ማመላለሸ በሆን ጊዜ ብቻ እንደሆነ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ለማጓጓዥ ያነት የዋለው የጭነት ተሽከርካሪ በሆነ ጊዜ ለአወራረስ ውሳኔው አሰጣጥ ባለንብረቱ ስለተጫነው ህገ ወጥ እቃ ያለውን እውቀት ወይም የወንጀል ተሳትፎ ማረጋገጥ አስፈላጊ ስለመሆኑ የተመለከተ ነገር የለም፡፡

በእርግጥ እነዚህ ድንጋጌዎች ስለተቆጣጣሪ አካሉ ስልጣን እና ተግባር በሚያተተው አንቀጽ 21 ስር የተመለከቱ ሲሆን የውርስ ውሳኔው በቀጥታ በዚሁ ተቆጣጣሪ አካል የሚሰጥ ስለመሆኑ በድንጋጌው የተመለከተ ነገር የለም፡፡ በሌላ በኩል የእነዚሁ ድንጋጌዎች ይዘት ቃል በቃል በሚባል ደረጃ ስለ ወንጀል ተጠያቂነት በሚደነግገው አንቀፅ 22/12/ ስርም ተደንግገው ይገኛሉ፡፡ አስተዳደራዊ የውርስ ውሳኔውን የመስጠቱ ስልጣኑም የጉምሩክ ኮሚሽን ስለመሆኑ በዚሁ ድንጋጌ ስር ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህ

ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መረዳት የሚቻለው የድንጋጌዎቹ መሰረታዊ ዓላማ ለህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ማጓጓዥ ያነት የዋለ ተሽከርካሪ በአዋጁ አንቀፅ 21/15 እና 16/ ድጋዎች መመዘኛ መሰረት የሚወረሱ መሆኑን፣ የመውረስ ውሳኔውም በጉምሩክ ኪሚሽን የሚፈፀም መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የአዋጁ አንቀፅ 21 ስለ ተቆጣጣሪ አካሉ ስልጣን እና ተግባር የሚዘረዝር እና ይኸው አካል የውርስ ውሳኔን ለመስጠት የሚችል ስለመሆኑ በድንጋጌው ያልተመለከተ በመሆኑ እነዚህ ድንጋጌዎች በማርቀቅ ሂደት በስህተት የተካተቱ መሆኑን ነው፡፡ ከድንጋጌዎቹ ይዘት እና በአዋጁ አንቀፅ 22 ስር ከሰፈረው ሀሳብ አኳያ የአዋጁ አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀጽ 15 እና 16 ድንጋጌዎች በአዋጁ አንቀፅ 22 ስር መካተት የነበረባቸው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ያም ሆኖ አላስፈላጊ ድግግሞሽ እንዲፈጠር ከማድረጉ ባለፈ የአዋጁ አንቀፅ 21 እና 22 ድንጋጌዎች ተጣምረው ሲነነቡ መሰረታዊ ሀሳባቸው ምን እንደሆነ ከላይ የተመለከተ በመሆኑ ከአፈፃፀም አኳያ የሚፈጥረው ችግር የለም፡፡

ከዚሁ ድንጋጌ ተግባራዊ አፈፃፀም ጋር በተያያዘም ይኸው ሰበረ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/241787 ላይ ሓምሌ 27/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት ለህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ማጓጓዥ ያነት የዋለው የህዝብ ማመላላሻ ተሽከርካሪ ካልሆነ በሌሎች ተሽከርካሪዎች የባለሀብቱን ተሳትፎ ወይም እውቅና መመርመር ሣያስፈልግ የጦር መሣሪያው መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ተሽከርካሪውም በጉምሩክ ኮሚሽን አስተዳደራዊ ውሳኔ መሰረት ውርስ ሆኖ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ሊወሰን እንደሚችል አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ከዚህ ችሎት የሚሰጥ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ደግሞ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ይህንኑ ችሎት ጨምሮ በማናቸውም ደረጃ በሚገኙ የፌደራልም ሆነ የክልል ፍርድ ቤቶች ላይ የአስገዳጅነት ኃይል ያለው ስለመሆኑ የፌዴራል ፍርድ ቤቶ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10 ይደነግጋል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ህገ ወጥ የጦር መሳሪያን ሲያጓጉዙ ተይዘዋል የተባሉት የአመልካቾች ተሽከርካሪዎች ደረቅ ጭነት ማመላለሻ አይሱዙ ተሽከርካሪዎች ስለመሆኑቸው የተገለፀ በመሆኑ ተሽከርካሪዎቹ ስለጫኑት ህገ ወጥ እቃ አስምልክቶ አመልካቾች የነበራቸው እውቀት ማጣራት ሳያስፈልግ በቀጥታ በተጠሪ መስሪያ ቤት በሚሰጥ አስተዳደራዊ ውሳኔ የውርስ ትዕዛዝ ሊሰጥባቸው የሚችል ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ይግባኝ ሰሚ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ የህጉን ይዘት እና ከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተከተለ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት መሰረታዊ የህግ ስህተት አልገተኘበትም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ በአበላጫ ድምጽ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 1ኛ አመልካችን በተመለከተ በመ/ቁ/227926 ላይ ታህሳስ 04/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ፣ እንዲሁም 2ኛ አመልካችን በተመለከተ በመ/ቁ/228134 ላይ ሚያዝያ 30/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነ ድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለ ግንዛቤ እንጂ ለፍር ዮ አ ረ ጸ ጸ ምዒለ ማአ የ ገ ለ ግል ም!

ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348/1/ እና በሰበር ስነ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡

2. የዚህ ፍርድ እና ውሳኔ ትክክለኛ ቅጂ ከመ/ቁ/249323 ጋር ይያያዝ፡፡

**ትዕዛዝ**

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡